

# አገልግሎቶቻችንን እንዴት እንደሚጠቀሙ

rtd-denver.com | 303.299.6000 | customercare@rtd-denver.com

ለዴንቨር ሜትሮ አካባቢ የሕዝብ መጓጓዣ አቅራቢ እንደመሆኑ መጠን፥ RTD በአውቶቡስ፥ ባቡር፥ Access-a-Ride (የአካል ጉዳት ላለባቸው ሰዎች አገልግሎቶች)፥ እንደ FlexRide ዓይነት የሠፈር ሚኒባሶች እና በሌሎችም አማካኝነት ማህበረሰቦችን ያገናኛል። የትራንስፖርት ፍላጎቶችዎን RTD እንዲያሟላልዎት ይፍቀዱ!

## የቅናሽ ዋጋ ፕሮግራሞች

እርስዎና ቤተሰብዎ ለቅናሾች ብቁ ሊሆኑ ይችላሉ። የዋጋ ቅናሽ ለሚከተሉት ማግኘት ይቻላል፦

- ዝቅተኛ ገቢ ያላቸው ሰዎች
- አዛውንቶች (ዕድሜያቸው 65+)
- የአካል ጉዳት ያለባቸው ሰዎች
- ወጣቶች (ዕድሜያቸው 19 እና ከዛ በታች የሆኑ)*

**ስለ ብቁነት ይበልጥ ለማወቅ እና ለቅናሽ ዋጋዎች ማመልከቻ ስለማስገባት የሚከተለውን ይጎብኙ rtd-denver.com/discount-fares!**

*ዕድሜያቸው 19 እና ከዛ በታች የሆኑ ወጣቶች በZero Fare for Youth (ለወጣቶች ዜሮ ዋጋ) ፕሮግራም አመራማሪነት በነጻ መጓዝ ይችላሉ።

## ቲኬቶች እና ማለፊያዎች እንዴት እንደሚገዙ

የሚጓዙት በአውቶቡስም ሆነ በባቡር፥ የRTD ቲኬቶችዎን እና ማለፊያዎችዎን መግዛት ቀላል ነው። ፍላጎቶችዎን የሚያሟላውን ታሪፍ ይምረጡ (የ3 ሰዓት፥ ዕለታዊ ወይም ወርሃዊ) እና ይቀጥሉ።

### ቲኬቶች እና ማለፊያዎች የት እንደሚገዙ

- በማናቸውም የባቡር ጣቢያዎች የሚገኙ የቲኬት መሸጫ ማሺኖች
- አውቶቡስ ነጂ (ጥሬ ገንዘብ ከተጠቀሙ ትክክለኛውን መጠን ይክፍሉ
- በrtdonlinestore.com ላይ
- የRTD ሽያጭ ማሰራጫዎች
- ተሳታፊ ኪንግ ሱፐርስ እና ሴፍዌይ ሱቆች




### በስማርት ስልክዎ ላይ RTD

ቲኬቶችን ለመግዛት ከሁሉም የሚቀለው ቦታ ብስልክዎ ላይ ነው። **RTD MyRide** መተግበሪያን ለ IOS ወይም ለአንድሮይድ ለማውረድ በስተቀኝ ያለውን QR ኮድ ስካን ያድርጉ።

**በrtd-denver.com ላይ የRTD አገልግሎቶችን ያስሱ፥ የጉዞዎን ዕቅድ ያውጡ እና ሌላም**

## ጉዞዎን ያቅዱ

ጉዞዎን ከመጀመሪያው እስከ መጨረሻው ለማቀድ፥ አውቶቡስዎ ወይም የባቡርዎ የት ጋር እንደደረሰ ለማየት፥ ወይም መዘግየቶችን ወይም ስረዛዎችን በቅጽበት ለማየት የRTDን **Next Ride** መሣሪያን (app.rtd-denver.com/nextride) ይጠቀሙ።

## አውቶቡስ ይውሰዱ

**ጠቃሚ ምክሮች**



- ፌርማታዎ ጋር ቀደም ብለው ይድረሱ።
- አውቶቡስ ሲመጣ፥ የማያስፈልግዎት መስመር እና መዳረሻ መሆኑን ለማረጋገጥ የላይኛው የፊት ክፍል ላይ ያለውን ዲጂታል ምልክት አይተው ያረጋግጡ!
- አውቶቡስ ላይ ተሳፍረው ዋጋውን በትክክለኛ ምንዛሪ፥ ወቅታዊ ቲኬት፥ ማለፊያ፥ MyRide ካርድ ወይም የሞባይል ቲኬት ይክፈሉ።
- የMyRide ካርድ ወይም የሞባይል ቲኬት የሚጠቀሙ ከሆነ በማረጋገጫው ስካን ያድርጉት።
- ወደ መዳረሻዎ ሲቃረቡ፥ እንዲቆምልዎት ለመጠየቅ ቢጫ ገመዱን ይጎትቱ ወይም መጫኛያውን ይጫኑ።
- ከተቻለ በኋለኛው በር ይውጡ።

## ባቡር ላይ መሳፈር

**ጠቃሚ ምክሮች**



- ጣቢያው ጋር ይድረሱ። ለቀጣዩ ባቡር ዲጂታል ምልክቶችን ወይም Next Rideን ይመልከቱ።
- ከመሳፈርዎ በፊት ቲኬት ወይም ማለፊያ ከመሸጫ ማሺኑ ይግዙ ወይም የሞባይል ቲኬትዎን ወይም ማለፊያዎን ዝግጁ ያድርጉ።
- የታተመ ቲኬትዎን በቀይ "V" ማሺኖች፥ የMyRide ካርድዎን በጥቁር እና በብርማ ማረጋገጫዎች ያረጋግጡ ወይም የሞባይል ቲኬትዎን እንዲሠራ ያድርጉ። ከቲኬት መሸጫ ማሺን የተገዙ ግዢዎችን ማረጋገጥ አያስፈልግዎትም።
- ባቡሩን ለመጠበቅ ከቢጫው መስመር ጀርባ ይቁሙ።
- ወደ መዳረሻዎ መቃረብዎን ለማወቅ የዲጂታል ምልክቱን ይመልከቱ ወይም የድምጽ ማስታወቂያውን ያዳምጡ።




## አውቶቡሶች እና ባቡሮች ላይ ደህንነትዎን ይጠብቁ

የሆነ ነገር ካዩ፥ የሆነ ነገር ይናገሩ። በRTD ሥርዓት ዙሪያ ስላሉ የደህንነት ስጋቶችን ሪፖርት ለማድርግ በግራ ያለውን QR ኮድ ስካን ያድርጉ እና የRTDን **Transit Watch** መተግበሪያን ያውርዱ። የደህንነት ስጋቶችን ለማሳወቅ በ303.299.2911 መደወል ወይም በ303.424.9100 ቴክስት ማድረግም ይችላሉ። ይበልጥ ለማወቅ rtd-denver.com/transitwatchን ይጎብኙ።

## እርዳታ እና የቋንቋ እገዛ

ስለ RTD ማንኛውም ጥያቄዎች ለመጠየቅ እባክዎ በ 303.299.6000 የደንበኛ እንክብካቤ ክፍል ይደውሉ። ትርጉም አገልግሎቶች በ200 በላይ ቋንቋዎች በነጻ ይገኛሉ። ለስፓኒሽ 2ን ይጫኑ። ለማንኛውም ሌላ ቋንቋ 8ን ይጫኑ። ከዚያም፣ ለወኪሉ የምትናገሩትን ቋንቋ ይግለጹ እና ከአስተርጓሚ ጋር እስከሚገናኙ በስልኩ ላይ ይቆዩ።

**የRTD አገልግሎቶችን ለማሰስ፥ ጉዞዎን ለማቀድ እና ሌሎችንም ለማየት rtd-denver.comን ይጎብኙ።**